STAY SAFE MN

# የኮቪድ-19 ውጤትዎን ሲጠብቁ ምን ማድረግ አለብዎት

## ከተመረመሩ ቡኃላ

- የሚከተሉት ካለቦት ቤት ውስጥ እና ከሌሎች ርቀው ይቀመጡ፡
  - ምልክቶች ካሉቦት
  - በቤትዎ ውስጥ ኮቪድ-19 የያዘው ሰው ካለ
  - ኮቪድ-19 ከያዘው ሰው ጋር አጠገብ ከነበሩ
- ምልክቶች ካልታዩቦት እና ኮቪድ-19 ከያዘው ሰው ጋር ቅርብ ካልነበሩ፣ በቤቶ ተቀምጠው ውጤቶን መጠበቅ አይኖርቦትም። ጭንብል ያድርጉ እና ከእርሶ ጋር ከሚኖሩ ሰዎች 6ጫማ ይራቁ። ማንኛውም ምልክቶች ማሳየት ከጀመሩ ቤትዎ ይቆዩ እና ከሌሎች ይራቁ ፡፡
- ፖዘቲቭ ውጤት ከመጣ ለ 10 ቀናት ያህል በቤት ውስጥ መቆየት ስለሚኖርቦ ምን እንደሚሰሩ ዕቅድ ያውጡ።
- በቅርብ ጊዜ ያገኙዋቸውን ሰዎች ዝርዝር ይጻፉ። ኮቪድ-19 ሊኖርቦት እንደሚችል እና ከእርሶ እስኪሰሙ ድረስ ከሌሎች እንዲርቁ ይንገሯቸው።
- የተመረመሩት ኮቪድ-19 ከያዘው ሰው ጋር ንክኪ ኖሮዎት ከሆነ እና ምንም ምልክት ከሌለቦት ምርመራው ኔጌቲቭ ቢመጣም በቤቶ ለ 14 ቀናት መቆየት ይኖርቦታል ምክኒያቱም አሁንም ሊታመሙ ስለሚችሉ።
- በቅርብ ለሚደረግ የህክምና ሂደት ከሆነ የተመረመሩት እና ምንም ምልክቶች ካላሳዩ ውጤትዎን በሚጠብቁበት ጊዜ በቤቶ መቆየት አይኖርቦትም።
- የምርመራዎ ውጤት እስኪመጣ ድረስ የተወሰኑ ቀናት ሊወስድ ይችላል። የምርመራ ውጤትዎ በኢሜል ፣ በአጭር የጽሁፍ መልዕክት እና/ወይም በስልክ ይደርሶታል።
- ምልክቶችን ይከታተሉ። ከባሱ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያናግሩ። የኮቪድ-19 ምርመራ እንዳደረጉ ይንገሯቸው።

## ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ

- በአሁኑ ጊዜ ኮቪድ-19 አለቦት ማለት ነው።
- **በቤ ይቆዩ።** የመንግስት ጤና ባለሞያ ይደውልሎታል። ስልኩን ማንሳቶ አስፈላጊ ነው። እንደ በቀጥታ ያገኟቸው ሰዎች ማን እንደሆኑ እና ስለ ጎበኟቸው ቦታዎች ያሉ ስለ ኮቪድ-19 ታጋላጭነት ጥያቄዎችን ይጠይቆታል።
- ምን ማድረግ እንዳለቦት እና ለስንት ጊዜ በቤት መቆየት እንዳለቦት የበለጠ መረጃም ይሰጦታል።

## ውጤትዎ ኔጋቲቭ ከሆነ

- በአሁኑ ጊዜ ኮቪድ - 19 **የለቦትም** ማለት ነው። ነገር ግን በማንኛውም ሰዓት ተጋላጭ ሊሆኑ ወይም ሊታመሙ ይችላሉ። እራሶን እና ሌሎችን ከኮቪድ-19 ለመጠበቅ እርማጃዎችን መውሰዶን መቀጠል አለቦት።
- የኮቪድ-19 ምልክቶችን ካዳበሩ ዶክተዎን ወይም ሌሎች የጤና ባለሞያዎችን ድጋሚ ስለመመርመር ያነጋግሩ።

## የበለጠ መረጃ

[የሚኒሶታ የጤና መምሪያ የኮቪድ-19 ድረገጽ](https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/)

https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/

**የሚኒሶታ የዕርዳታመስመር 651-297-1304 ወይም 1-800-657-3504**
(ከሰኞ እስከ አርብ: 9 a.m. እስከ 4 p.m.).

MINNESOTA

Minnesota Department of Health | health.mn.gov
651-201-5000
የተለየ ቅርጸት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ን ያግኙ።

11/17/2020 (Amharic)